## የምድሩን ቤታችን ሰርተን ስናሳምር(ተስፋሁን ሞላ)



የምድሩን ቤታችን ሰርተን ስናሳምር
ይህው ጥለናት ሄድን ደስ ብሎን ሳንኖር
ያከማቸነው ወርቅ የሰበሰብነው ብር
አብሮነም አልሄደ ስንወርድ መቃብር።
ሶስት ክንድ ቁራጭ ናት ለኛ የበቃችን
በእሷ ተጠቅልለን ከራስ እስከ እግራችን
ወደ ማይቀረው ሄድን ከዓለም ተለይተን።
ሁሌ ተሸሽገን በሰማይ በምድር
ከሶስቱ ሥላሴ ከፈጠረን እግዜር።
ጥሩ ሥራ አልሰራን ከእሱ የሚያቀርበን
የማያልፈውን ፤በሚያልፍ ቀይረን።
ከባለ ጸጋው ከነነዌ፤ የሰው ልጅ ምን ይማር
በምድር እያለ ለድሃ አላበላ እሱ ጠግቦ ሲያድር
በላይ በሰማይ ሲያልፍለት አልአዛር
እሱ ግን ተጓዘ ወደ ሲኦል ባሕር።
የምድሩን ቤታችን በወርቅ ሥንሰራ
ድኃን እየበደልን ለሰው ሳንራራ
ሃያ አንድ ዓመት ሙሉ ስናደርግ ጭፈራ
አባትና ልጅ ተቀምጠን በሁለት ጎራ
በሀገር በሃይማኖት አመጣን መከራ።
አልበቃን ቢል የያዝነው ንብረት
ልንዘርፍ  ገብተን ከፈጣሪ፤ ቤት
ተይዘን ታሰርን  በእሳት ሰንሰለት
ያውም በሳጥናኤል በሌለው ምህረት።
የእኔ ጓደኞች ያላችሁ በምድር
ንስሐ ግቡና ታረቁ ከእግዚአብሔር
አልጠቀመም ለእኛ የያዝነው ወርቅ፤ ብር።
ስቆራርጥ ኑሬአልሁ የሰው አካል በፈንጅ
የእጄን አገኛለሁ በላይ በሰማይ ደጅ
ሰው አታስቸግሩ ብልችሁ አልቅሱ በግዳጅ
ለመጣ ለሄደው ለሁሉም አልፎ ሃጅ
እኔስ ገብቻለሁ ማቀዝቀዣ ፍሪጅ
እንኳንስ በድኔ ህይወቴም አልነበራት ወዳጅ።
የአላማ ጓዶቼ እኔን ተመልከቱኝ
ከባሕር ላይ ቁሜ እሳቱ ሲበላኝ።